SmaRT Ethiopia

INITIATIVE ON
Sustainable Animal Productivity

Photo: ILRI//Apollo Habtamu

አጭር የፖሊሲ መግለጫ | ለተሻሻለ ሥነ-ባህርይ እና የእንሰሳት ጤና ለአውራ በጎች እና ፍየሎች የጥራት ማረጋገጫ መስጠት

ቁልፍ መልዕክቶች

- ለዕርባታ የሚሆኑ ጥራት ያላቸዉን አውራዎች መለየትና ማወቅ የማንኛውም የዝርያ ማሻሻያ ፕሮግራም ወሳኝ ተግባር ነው። ከማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የተገኙትን የተሻሻሉ ዝርያ ያላቸዉን አውራ በጎችንና ፍየሎች ማሰራጨት የሚቀጥለው ትውልድ የተሻለ የዘር ውርስ እንዲኖረው እና የተሻለ ምርትን ለማግኘት ወሳኝ ነው።
- መደበኛና ተከታታይነት ያለው የአውራ ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት አሠራርን መከተል ከፍተኛ የምርታማነት አቅም፣ ከበሽታ ነጻ እና ጥሩ የማጥቃት ብቃት ያላቸው አውራዎች በጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ከመጥቀሙም በላይ የአርቢዎችን የምርት ጥራት (brand) ለመጠበቅ እና ለገዥዎች የጥራት ዋስትና ለመስጠት ይረዳል።
- የአዉራዎች ጥራት የማረጋገጫ ፕሮግራም አዋጭነትንና ታማኝነትን የሚወስነው የሕዝብ እና የግል አጋርነትን ጨምሮ ዘላቂ ተቋማዊ አደረጃጀቶች ሲኖሩ ነው።
- የእርባታ የህብረት ሥራ ማኅበራት እና ሌሎች ማህበራት የበለጠ የራስ ገዝ አስተዳደር ስልጣን እስኪያገኙ ድረስ ለጥራት ማረጋገጫ የሚያወጡት ወጪ በህዝብ ድጋፍ መደገም አለበት።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

በኢትዮጵያ ማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች በሚገባ በተተገበሩባቸው ቦታዎች የበግ እና የፍየል ዝርያዎች ከፍተኛ የዘረመል ጥቅሞችን አስገኝቷል። ከነዚህ የእርባታ መርሀ ግብሮች የተገኙ የላቀ ሥነ-ባህርይ ያላቸው አዉራዎች በዚያው በተገኙበት የማህበረሰቡ መንጋዎች ላይ በጥቅም ላይ ይውላሉ። የተመረጡ አውራ በጎች እና ፍየሎች በጥቅም ላይ ከመዋላቸው ወይንም ከመሸጣቸው ወይንም ከመለወጣቸው በፊት አስፈላጊውን ባህርያት መያዛቸውን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት በማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች ማዕቀፍ ለተሰራጩት አውራዎች የጥራት ዋስትና ለመስጠት የመጀመሪያ ዘዴ ነው። ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ የአገር ውስጥ ዝርያዎችን ማሻሻል አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም እንዲኖር ያበረታታል። ለዚህ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት የዓለም አቀፍ የደረቃማ አካባቢ ምርምር ማእከል (ICARDA) እና የዓለም አቀፍ የእንሰሳት ምርምር ተቋም (ILRI) በኢትዮጵያ ከሚገኙ አጋሮቻቸው ጋር በመሆን የማረጋገጫ አሠራር ሂደት በጋራ ነድፈዉ በጋራ በመተግበር ላይ ይገኛሉ። ይህ የአሠራር ሂደት የዘረመል አቅምን፣ የማጥቃት ችሎታን እና የአውራውን የጤና ሁኔታ መገምገምን ያካትታል። ይህንን የአሠራር ሂደት በስፋት ለማከናወን የሚያስችሉ ልምዶች ተገኝተዋል። በተጨማሪም የጥራት ማረጋገጫ መስጠት የህዝብ ጥቅም ጉዳይ ስለሆነ የአሠራር ሂደቱን ለመደገም የህዝብ የገንዘብ ድጋፍ መኖር አለበት።

በ10ኛው ዓመት የማህበረሰብ አቀፍ የበጎችና ፍየሎች የህብረት ሥራ ማህበራት በዓል ሲከበር አየለች አለቶ አሸናፊ ከሆነው በጎ ጋር።

ILRI INTERNATIONAL LIVESTOCK RESEARCH INSTITUTE

ICARDA Science for resilient livelihoods in dry areas

መግቢያ

ኢትዮጵያ በዓለም ውስጥ ከፍተኛ የበግ እና የፍየል ቁጥር ያላት ሀገር ናት። አገሪቱ 42.9 ሚሊዮን በጎችና 52.5 ፍየሎች እንዳሏት የ2021 የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን መረጃ ያሳያል። ይሁን እንጂ በምርታማነት እና የስጋ ምርት ደረጃ በአገር ውስጥ ሊያስገኙ ከሚችሉት ገቢ በጣም ያነሰ ሲሆን ወደ ውጭ የመላኩ ሁኔታ የተመቻቸ አይደለም። ለዚህ ሁኔታ መኖር እንደ አንድ ችግር የሆነው ትናንሽ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ምርታማ የሆኑ፤ የተመረጡ እና በሚገባ የተላመዱ የአገር ውስጥ በጎችን እና ፍየሎችን የሚያገኙባቸው የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች ባለመኖራቸው ነው።

ይህንን ችግር ለመቅረፍ የማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች በዓለም አቀፍ የደረቃማ አካባቢ ምርምር ማዕከል እና በአጋሮቹ ካለፉት አሥር ዓመታት ጀምሮ በመላው በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች እየተተገበሩ ናቸው። የማኅበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃግ ብሮች በአግባቡ በተተገበሩባቸው ቦታዎች ማኅበረሰቡ የዘር ዉርስ እና ሌሎች ተዛማጅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች አግኝቷል። (Haile et al, 2020)

Photo ILRI/Apollo Habtamu

ዓለማየሁ ሃይሌ በቦንጋ የሚገኝ አንድ ማህበረሰብ አቀፍ የእርባታ የህብረት ሥራ ማኅበር ተወካይ ናቸው። በምስሉ ከማህበረሰቡ የተገኘውን በግ የሰውነት ሁኔታ ሲፈተሹ ይታያል።

አቀራረቡ እና ውጤቶቹ

የአውራ በግ/ኮርማ ፍዩል የጥራት ማረጋገጫ የአሠራር ሂደት የሚከተሉትን ያካትታል። (ምስል 1ን ይመልከቱ)

- **ደረጃ 1፡-** ማረጋገጫ የሚሰጣቸው አውራዎች በማህበረሰብ የዝርያ ማሻሻያ መርሃግብሮች በተመራማሪዎችና የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማኅበር ውስጥ በተሰየመው ኮሚቴ አማካይነት ተለይተው ይቀርባሉ።

- **ደረጃ 2፡-** አውራዎች በአካባቢው በሚገኙ እና የማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን አሠራር እየተተገበሩ ባሉ የምርምር ተቋሞች ውስጥ ይገመገማሉ። አውራዎቹ የሚገመገሙት የተቋሙን የመራቢያ መረጃ የአስተዳደር ሥርዓት መሠረት በማድረግ በተዘጋጁ የመራቢያ ዋጋ ግመታ እና የተመረጡ ባህርያት ነው። በዚህ ደረጃ የሚገኝን ስራ በመጨረሻ ለብሔራዊ የእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ተቋም (NAGII) ማስረከብ ያስፈልጋል።

- **ደረጃ 3፡-** በአውራዎቹ ላይ የአካል ምርመራ፤ የህክምና ምርመራ፤ የዘር ፈሳሽ ምርመራ እና የማጥቃት ብቃት ግምገማ ይካሄዳል። ይህን የሚያደርጉት የሰለጠኑ የክልሉ የምርምር ማዕከል ቡድኖች ከአጎራባች የእንሰሳት ጤና አገልግሎቶች ጋር በመተባበር ነው።

ከማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች መጠቀም በዋናነት የተመረጡ አዉራዎች ብዙ ቁጥር ያላቸውን እንስቶችን እንዲያጠቁ ማድረግ ያስችላል። ይህን ማድረጉ ወንዶቹ የዘረመል የበላይነት ያለውን ዘሮቻቸውን ወደ ብዙዎቹ በማስተላለፍ የዘረመል ዕድገት እንዲፈጋጥ ያደርጋል። የዘር ዉርሳቸዉን ለማሻሻል የተመረጡ አውራዎች የማጥቃት አካላዊ ብቃት ያላቸው እና በማጥቃት ጊዜ ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ የሆኑ መሆን አለባቸው።

ህጋዊ የአውራዎች ማረጋገጫ መርሃ ግብር ተጠቃሚዎች ትክክለኛውን አውራ እየተጠቀሙ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ይሰጣል። የማረጋገጡ ሂደት ሳይንሳዊ ግምገማን፣ ብዙ ተቋማትን ሊያሳትፍ የሚችል ተቋማዊ ዝግጅት፡ሂደቱን እና ትግበራውን የሚመሩ የፖሊሲ እርምጃዎችን ይጠይቃል። የአለም አቀፍ የደረቃማ አካባቢ የምርምር ማዕከል (ICARDA) እና አጋሮቹ በተፈጥሮ መንገድ ወይንም በሰው ሰራሽ ማዳቀል ዘዴዎች በጥቅም ላይ ለሚውሉ አውራ በጎችና ፍየሎች ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር አዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶች እና ግንዛቤዎች ከትግበራው የተገኙ ሲሆን ይህንኑ ሂደት በሌሎች የእንሰሳት ዝርያዎች ላይ መጠቀም ይቻላል።

Photo ICARDA/Tesfaye Getachew

የመንዝ ምርጥ የርቢ አውራ በግ በኢትዮጵያ

- **ደረጃ 4፡-** የሚመለከተው የክልሉ የእንሰሳት ጤና ክፍል አውራዎቹን በወቅቱ በአካባቢ ካሉ የመራቢያ በሽታዎችን የሚከላከሉ ክትባቶችን ይከትቧቸዋል።

- **ደረጃ 5፡-** በዚህ ደረጃ ውስጥ ብቁ ሆነው ለተገኙ አውራዎች የመጨረሻው ማረጋጫ ይሰጣቸዋል። (ምስል 2ትን ይመልከቱ) ቴክኒካዊው ግምገማ መሠረት ማረጋገጫውን የሚሰጣቸው የግብርና ወይንም የእንሰሳት ልማት ጽ/ቤት ነው። (ምስል 3ትን ይመልከቱ)

የመረጃ ትንተናው፤ የተለያዩ ሳይንሳዊ ግምገማዎች እና ክትባቶችን የመስጠት ስራዎች ወጪ ያስወጣሉ። ስለሆነም የማረጋገጡ ሂደት እራሱን ችሎ መስራት እስኪችል ድረስ የህዝብ የድጎማ ድጋፍን ማግኘት አለበት። ሆኖም በሰው ሰራሽ የማዳቀል መርሃ ግብሮች የተገኙ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው እንሰሳት በሚያስገኙት ገቢ ወጭውን በመጠኑም ቢሆን መደጎም ይቻላል። በአንዳንድ ማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች በተተገበረባቸው ቦታዎች የዓለም አቀፍ የደረቃማ ምርምር ማዕከል (ICARDA) እና አጋሮቹ ተንቀሳቃሽ እና ለዝቅተኛ መሠረተ ልማት የሚሆኑ የሰው ሰራሽ ማዳቀያ ጣቢያዎችን መስርተዋል። እስካሁንም የተጣራ ትኩስ የዘር ፈሳሽን በመጠቀም ተቀባይነት ያለው የመራባት ውጤት ተገኝቷል።

ምስል 1- በአውራ በጎችና ፍየሎች የማረጋገጫ ሂደት ውስጥ ያሉ ደረጃዎችና ተሳታፊዎች

ምንጭ፡- ዓለም አቀፍ የደረቃማ አካባቢ ጥናት ማዕከል (ICARDA) - ለቢ-ሲ--ቪ-ኤ (BCVA) እና በሰኔ 2014 ኤድንበርግ ውስጥ በባለሙያዎች አውደ ጥናት ለተሳተፉ የበጎች ህክምና ማህበር አባላት ተጨማሪ ምስጋና እናቀርባለን።

አስተማማኝ እና እምነት የሚጣልባቸዉ አውራ በጎች እና ፍየሎችን ማራባት በኢትየጵያ



ምስል 2- በኢትዮጵያ ውስጥ በቦንጋ የተሰጠው የአውራ በግ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ሞዴል

ምንጭ፡- ዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ የምርምር ማዕከል ለቢ-ሲ-ቪ-ኤ (BCVA) እና በሰኔ 2014 ኤድንበርግ ውስጥ በባለሙያዎች አውደጥናት የበግ ህክምና ማህበር አባላት ተጨማሪ ምስጋና እናቀርባለን።



ዕድሜ

የተገመተ የእርባታ ዋጋ

የአውራ በግ ቅድመ እርባታ ምርመራ ሰርተፍኬት (የቦንጋ ማኅበረሰብ አቀፍ የእርባት መርሀ ግብር)

ምርመራ የተደረገበት ዕለት፡- _____

ግብርና ሚኒስቴር MINISTRY OF AGRICULTURE

ICARDA

ደ ን ም ኢ ETHIOPIA

SARI 2001

1. የአካል ምርመራ

የሰውነት ሁኔታ ውጤት (1-5)		
አይኖች አፍንጫ አፍ	እንከን አልተገኘም	እንከን አለበት
መመሳሰልና የእጅና የእግር ጤናማነት		
እግሮች		
ውጫዊ ብልት		
ሽክርክሪት ዙሪያ (scrotal circumference)	cm	
አጠቃላይ ውጤት፡- አጥጋቢ/ አጥጋቢ ያልሆነ		

እንደአስፈላጊነቱ ተገቢውን ምልክት ያድርጉ።

2. የዘር ፈሳሽ ምርመራ

የማሰባሰብ ዘዴ	ሰሠሴብ*	በኤየወዘመ**
የፈሳሽ መልክና ውፍረት	/5	
አጠቃላይ እንቅስቃሴ	/5	
አጠቃላይ ውጤት አጥጋቢ የሆነ / አጥጋቢ ያልሆነ		

ሰሠሴብ* - ሰው ሠራሽ የሴት ብልት

በኤየወዘመ** - በኤሌክትሪክ የሚሰራ የወንዴ ዘር መርጫ

3. የማጥቃት ብቃትና ፍላጎት ግምገማ

ይህ አውራ በግ መደበኛ የሆነ አገልግሎት የመስጠት ባህርይ እና የማጥቃት ብቃት ሲያሳይ ታይቷል።	
ይህ አውራ በግ መደበኛ የሆነ አገልግሎት የመስጠት ባህርይ እና የማጥቃት ብቃት ሲያሳይ አልታየም።	

በትክክለኛው አማራጭ ላይ ምልክት ያድርጉ።

4. የዓይነት በዓይነት ምደባ

ለማራባት ተስማሚ ነው።	በክፍል 1 የተቀመጡትን መስፍረቶች ብቻ በሚሟላቱ።
ለማራባት ተስማሚ ነው።	በክፍል 1 እና 2 የተቀመጡትን በስፈርቶች ብቻ በሚሟላቱ።
ለማራባት ተስማሚ ነው።	በክፍል 1፣ 2 እና 3 የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚሟላቱ።
ለማራባት ተስማሚ አይደለም።	

የወረዳ የእንሰሳት እርባታ ጽ/ቤት ኃላፊ ቀን	ፊርማና ማኅተም

ቦንጋ

የመስክ ላይ መረጃ ስብሰባ ቅፅ
(የዶሮገና ማኅበረሰብ አቀፍ የዝርማሻሻያ መርሃግብር)

በእያንዳንዱ ባዶ ሳጥን ውስጥ ምልክት፣ ልኬት፤ አስተያየት ወይንም አልተመረመረም የሚል መግለጫ መኖር አለበት።

የውልደት ቀን / እድሜ (ወራት)			
የሰውነት ሁኔታ ውጤት (ከ5 ነጥብ)			
ጤነኛ ከሆነ 'ጤነኛ' ይፃፉ። ጤነኛ ካልሆነ ለምሳሌ 'ትንሽ፣ የሰፋ፣ ለስለሳ፣ ጠንካራ፣ ጎበጥ ያለ፣ ያበጠ ወዘተ...' በማለት ይግለፁ።	ጥርስ		
	እግር		
	ቀሪ አካል		
	ደረት		
	ሸለፈት		
	የወንድ ብልት		
	ቆለጥ		
	የዘር ፍሬ መጠን	ግራ	ቀኝ
	ቆለጥ ቋር ራስ	ግራ	ቀኝ
	ቆለጥ ቋር ጅራት	ግራ	ቀኝ
የቆለጥ ዙሪያ በሴ.ሜትር			

የወንድ ዘር ፍሬ የመሰብሰብ ዘዴ	የመጀመሪያ ስብሰባ		ሁለተኛ ስብሰባ	
መጠን (ሚሊ ሊትር)	ሰሠሴብ*	በኤየወዘመ**	ሰሠሴብ*	በኤየወዘመ**
አጠቃላይ እፍጋት 0 (ግልፅ) - 5 (ድርብ አይባም)				
አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሞገድ እንቅስቃሴ (0-5)				
የማጥቃት ችሎታ				

ክትባት	ዕለት
ብሩሰሎሲስ (brucellosis)	
የበግ/ፍየል ፈንጣጣ	
የበግ እና የፍየል ቸነፈር (peste des petits)	
የእግር እና የአፍ ሕመም	
ኤንትሮቶክሳሚያ (enterotoxaemia)	

ሰሠሴብ *- ሰው ሠራሽ የሴት ብልት በኤየወዘመ**- በኤሌክትሪክ የሚሰራ የወንዴ ዘር መርጫ

ምስል 3 - የአውራ በጎች እና ፍየሎች ማረጋገጫ የመስክ ላይ ግምገማ መስፈርቶች

ምንጭ፡- ዓዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ የምርምር ማዕከል የአውራ በጎች የቅድመ መራባት ምርመራ

አንደምታዎችና ምክረ ሀሳቦች

ከማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ የተገኙትን አውራዎች ጥሩ የሆነ አጠቃቀም የሚወሰነው የበላይነት አላቸው ተብለው በተመረጡት አውራ በጎች እና ፍየሎች ላይ ነው።

- ለአውራዎች የጥራት ማረጋገጫ ማስረጃ የምስክር ወረቀት መስጠት አርቢው ማህበረሰብና ገዥዎች በዘረመል የላቁ፣ የአካል ብቃት ያላቸውን ከተላላፊ በሽታዎች የተጠበቁ፣ የፈሳሽ ዘር ጥራትና የመሰረር ብቃት ያላቸውን እንሰሳት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።
- ለሰው ሰራሽ ማዳቀል ማረጋገጫ የተሰጣቸውን አውራ በጎች እና ፍየሎች መጠቀምን ማስተዋወቅ ለዘረመል መሻሻል አስተዋፅዖ ከማድረጉም በላይ ለሥራው የወጣውን ወጪ ለመሸፈን ይረዳል። በሰው ሠራሽ ማዳቀል ሆነ በተፈጥሮ ግንኙነት በጥቅም ላይ ለሚውሉ አውራዎች የማረጋገጫ ሂደት ውስጥ የተለየ የደረጃ አሰጣጥ ሥርዓት መከተል ሊያስፈልግ ይችል ይሆናል። ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ ለማረጋገጫው ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል።
- የማረጋገጫውን ሂደት ታማኝነት የበለጠ ለማጠናከር በዋጋ ግመታ፣ የመራቢያ ውጤቶችን የመገምገም ምርመራ ትክክለኛነት እንዲሁም በተለያዩ ዝርያዎች መካከል ተመሳሳይነትን ለመጠበቅ በብሔራዊ ደረጃ የተቀናጀ እርምጃና ድጋፍ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን የምርምር ተቋሞች እንደተጨማሪ ስራ በማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች ስራውን ለማከናወን በሚያስችል አቋም ላይ ቢሆኑም የማረጋገጫው ፕሮግራም ኃላፊነት በግብርና ሚኒስቴር የእንሰሳት ምርት ክፍል እና በብሔራዊ የእንሰሳት ልማት ተቋም ውስጥ የሚካተት ነው። የCGIAR ማዕከሎች ማለትም ዓለም አቀፍ የደረቃማ አካባቢ ምርምር ማዕከል እና ዓለም አቀፍ የእንሰሳት ምርምር ተቋም ፕሮግራሙን አሁን በሥራ ላይ በተሰማሩት ተቋማት ለብዙ ጊዜያት ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ ወደሚችሉ አካላት ለማዛወር የሚደረገውን ሽግግር ለማበረታታት ይችላሉ።

- ለማህበረሰብ አቀፍ የዝርያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የሚደረገው የአውራ ማረጋገጫ አሰጣጥ ሂደት ለህዝብ ጥቅም የሚከናወን ስራ በመሆኑ በህዝብ ሥርዓት መደገፍ አለበት።
- የሰው ሰራሽ ማዳቀልን በጥቅም ላይ ለማዋል ለሚውሉ ምርጥ አውራ በጎች እና ከነሱ የሚቀጥል ደረጃ ላላቸው በተፈጥሮ ሁኔታ ለሚያጠቁ ኮርማዎች የዋጋ ማበረታቻዎችን መስጠት ገሚሱን የማረጋገጫ ወጪ ለመሸፈን ያስችላል። የማረጋገጫ ዋጋ ወጪ የማስፋፋት ሂደቱንና የተሻሻሉ አውራዎችን በሰፊው በመጠቀም ላይ እንቅፋት ስለሚችል ሂደቱን በከፊል በገንዘብ መደገፍ ያስፈልጋል።
- የሂደቱን ታማኝነት ለማረጋገጥ የሚደረጉ ተቋማዊ ዝግጅቶች በተለይ የክትባትን እና የዘር ፍሬ ምርመራን ወጪ ጫና የሚያቃልሉ ዘዴዎች እና በሰው ሰራሽ የማዳቀል ወይንም በተፈጥሮ መንገድ ለሚያስወልዱ የተረጋገጠላቸው አውራዎች የተለያየ ዋጋ መተመን አሁንም ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው።

Photo ICARDA/Tesfaye Getachew

ህፃናት ሴት ፍየሎቻቸውን ይዘው በአንድ ተዘዋዋሪ ሰው ሠራሽ ማዳቀያ ጣቢያ ተራቸውን ይጠባበቃሉ፡ ሴት ፍየሎቹ ማረጋገጫ ከተሰጠው አውራ የተገኘ የወንድ ዘር ፍሳሽ ይዳቀላሉ።

Photo ICARDA/Tesfaye Getachew

ማረጋገጫ የተሰጠው የፍየል ኮርማ በኮንሶ። እነዚህ ኮርማዎች በአካባቢው በተካሄደው የሰው ሠራሽ ማዳቀል ዘመቻ ውጤቶች ሲሆኑ ማህበረሰቡ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸው ናቸው።

ማጣቀሻዎችና ተጨማሪ ንባቦች

CSA.2021. Federal Democratic Republic of Ethiopia Central Statistical Agency Agricultural Sample Survey 2020/21 [2013 e.c.] Volume II Report on Livestock and Livestock Characteristics (Private Peasant Holdings)

Haile, A., Getachew, T. , Mirkena, T., Duguma, G., Gizaw, S., Wurzinger, M., Soelkner, J., Mwai, O., Dessie, T., Abebe, A., Abate, Z., Jembere, T., Rekik, M., Lobo, R.N.B., Mwacharo, J.M., Terfa, Z.G., Kassie, G.T., Mueller, J.P. and Rischkowsky, B. 2020. Communitybased sheep breeding programs generated substantial genetic gains and socioeconomic benefits. Animal 14(7):1362–1370.

Rekik, M., Getachew, T., Haile, A., Rischkowsky, B. 2021. Field solution for artificial insemination of sheep and goats in low input systems. SmaRT Ethiopia Brief. Nairobi, Kenya: ILRI. https://hdl.handle.net/10568/117433

ምስጋና

ይህ ምርምር፣ ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር አማካሪ ቡድን (CGIAR)፣ በእርባታ እንስሳት ላይ በሚያካሄደው የምርምር መርሃ-ግብር ውስጥ ሲደረግ ቆይቶ፣ በCGIAR ዘላቂ የእንስሳት ምርታማነት ኢኒሼቲቭ ውስጥም ቀጥሏል። የCGIAR ምርምር የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከCGIAR Trust Fund አስተዋፅዖዎች ነው። CGIAR የምግብ ደህንነቱ የተረጋገጠበት መጪ ዘመን እንዲፈጠር የሚሠራ ሉላዊ የምርምር ሕብረት ሲሆን፣ በአየር ሁኔታ ቀውስ ውስጥ የምግብን፣ የመሬትን፣ እና የውሃን ሥርዓቶች ለማሻሻል በቁርጠኝነት ይተጋል። በተጨማሪም፣ እነዚህ የምርምር ወረቀቶች ወደአማርኛ እንዲተረጎሙ እና የገፅ ንድፋቸው እንዲሠራ፣ የCGIAR የአየር ሁኔታ ምርምርን ተፅዕኖ ማቀለጠፍ ለአፍሪካ (AICCRA) ለተሰኘው ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገው የዎርልድ ባንክ አካል ለሆነው ዓለም-አቀፍ ልማት ማኅበርም (IDA) ምስጋና እናቀርባለን።

አጋሮች

ስማርት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) እንዲሁም ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር እንስቲትዩት (NARS) ጋር በመተባበር በዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ ምርምር ማዕከል (ICARDA) የሚመራ ነው።

ፀሐፊዎች

Mourad Rekik, Tesfaye Getachew, Aynalem Haile and Barbara Rischkowsky (ICARDA)

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት

Mourad Rekik, ICARDA / m.rekik@cgiar.org
Tesfaye Getachew, ICARDA /t.getachew@cgiar.org

ይህን ህትመት ለመጠቀም ፍቃድ የሚሰጠው the Creative Commons Attribution 40 በተባለ ዓለም አቀፍ ፈቃድ ሰጭ በኩል ነው። ኦክቶበር 2021